የ29ኛ ዓመት ቁጥር 192

አሶሳ፣ ህዳር 7 /2015 ዓ.ም

# የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

# ልሣነ-ሕግ ጋዜጣ

# LISAN HIG GAZETA

ፖ. ሳ.ቁጥር 293

ያንዱ ዋጋ.--------

**Of the Council of the Benishangul Gumuze Regional State**

**በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት**

**ጠባቂነት የወጣ ደንብ**

---

## አዋጅ ቁጥር 192/2015 ዓ/ም

## የቤ/ጉ/ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 170/2012 ዓ.ም ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የአካባቢ አስተዳደሮች የተሰጣቸውን ራስን በራስ የማስተዳደር ተግባር ተጠቅመው ህብረተሰቡን በማነቃነቅ የህዝቡን ተሳትፎና የውሳኔ ሰጪነት ሚናን በማጉልበት በሰው ኃይል፣ በበጀትና በአሠራር ራሳቸውን በማጠናከር ለልማቱ መፋጠንና ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

የአካባቢ አስተዳደሮች በየጊዜው የሚኖረውን የአጠቃላይ የህዝብ ቁጥር መጨመር እና የማህበራዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሻሻል ተገቢ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 (1) ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## አንቀጽ 1

## አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ *"ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 170/2012 ዓ.ም ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 192/2015 ዓ.ም "*ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 2

## ማሻሻያ

ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣ በአዋጅ ቁጥር 170/2012 ዓ.ም አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2(ሠ) የመንጌ ወረዳ ስር ከተዘረዘሩ 19 ቀበሌዎች በተጨማሪ *ኦፓ ቀበሌ፣ ፀላንገር ቀበሌ እና አሹመን ቀበሌ በአዲስ እራሳቸውን ችለው ተደራጅተው ተጨማሪ ቀበሌ በማድረግ የመንጌ ወረዳ ጠቅላላ ቀበሌ ቁጥር 22 እንዲሆን ተደርጓል፡፡*

## አንቀጽ 3

## አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከጸደቀበት ህዳር 07/2015 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

አሶሳ፣

ህዳር 7 / 2015 ዓ.ም

አሻደሊ ሀሰን አልአጀብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት